

# በኮቪድ-19 ወቅት የቤት እንስሳዎችዎን ደህንነት መጠበቅ

## ኮቪድ እና እንስሳቶች

ኮቪድ-19ን ስለሚያመጣው ቫይረስ ገና እየተማርን ቢሆንም፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከሰው ወደ እንስሳት ሊተላለፍ እንደሚችል ማሳያ አለ። እንዳንድ የቤት ውስጥ እንስሳዎች፣ ውሻዎችን እና ድመቶችን ጨምሮ፣ የኮቪድ19ን ለሚያመጣው ቫይረስ ምርመራ ሲደረግባቸው በሰውነታቸው ውስጥ ተገኝቷል፣ ይህም በብዛት የሆነው በኮቪድ-19 ከተይዘ ሰው ጋር የቀርብ ግንኙነት ከፈጠሩ በኋላ ነው።

በሽታው ወደሰውነታቸው ውስጥ የገባ የቤት እንስሳቶች ሊታመሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን አብዛኛዎቹ መለስተኛ ህመም ብቻ የሚኖራቸው ሲሆን ሙሉ በሙሉም ያገግማሉ። አብዛኛዎቹ በሽታው በሰውነታቸው ውስጥ የገባ የቤት እንስሳቶች ምንም ምልክት አያሳዩም።

በአሁኑ ሰአት የቤት እንስሳቶች የኮቪድ-19 ህመም ወደ ሰዎች እንበሚያስተላልፉ ምንም ማስረጃ የለም።



## የኮቪድ-19 ህመም ካለዎት ወይም ለኮቪድ-19 ከተጋለጡ፣

በቤትዎ ውስጥ ላለ ለሌላ የቤተሰብ አባል የሚያደርጉትን አይነት ጥንቃቄ ለቤት እንስሳዎችዎ በማድረግ በበሽታው እንዳይያዙ ይከላከሉ።

- ለቤት እንስሳዎችዎ ሌላ የቤተሰብ አባል እንክብካቤ እንዲሰጥ ያደርጉ።
- የቤት እንስሳዎችዎት በቤት ውስጥ እንዲቆዩ እና፣ ከተቻለ ደግሞ፣ እንደልብ እንዳይንቀሳቀሱ ያድርጉ።

## ለቤት እንስሳዎት የግድ እንክብካቤ መስጠት ካለብዎት

- የቅርብ ንክኪ (ማሻሻት፣ መሳም፣ በአንድ አልጋ ውስጥ አብሮ መተኛት) አያድርጉ።
- እነርሱ አካባቢ ማስክ ያድርጉ።
- ቅድምን ድሕርን ንፃኦም ምክንኻን ወይ ድማ ናቶም ኣቕሑ ድሕሪ ምትንካፍኩም ኣእዳውኩም ተሓጸ (መግቢ፡ ሽሓንታት፡ ባምቡላታት ወዘተ።)።

UNIVERSITY of WASHINGTON

Center for One Health Research

deohs.washington.edu/cohr

HEALTH SCIENCES LIBRARY

UNIVERSITY of WASHINGTON

University Libraries

hsl.uw.edu

*Developed resources reported in this publication are supported by the National Library of Medicine (NLM), National Institutes of Health (NIH) under cooperative agreement number UG4LM012343 with University of Washington. The content is solely the responsibility of the authors and does not necessarily represent the official views of the National Institutes of Health.*

## የቤት እንስሳዎት ምልክት ካለው

በቤት እንስሳት ላይ የሚታዩ ምልክቶች ማሳል፣ ማስነጠስ፣ ድካም፣ ለመተንፈስ መቸገር፣ ትኩሳት፣ ከአፍንጫ ወይም ከአፍ ፈሳሽ መውጣት፣ ማስመለስ፣ ወይም/እና ተቅማጥን ያካትታሉ። እነዚህ ምልክቶች በብዛት ኮቪድ-19 ባልሆኑ በሌሎች በሽታዎች ነው የሚመጡት፣ ነገር ግን እንስሳዎት የታመመ ከመሰለ፡

- የእንስሳት ሃኪም ጋር ይደውሉ።
- ከሌሎች እንስሳቶች አርቀው ያስቀምጧቸው።

ምንም እንኳን አሁን ላይ ጤነኛ ቢሆኑም፣ እንስሳዎትን ወደ እንስሳት ክሊኒክ ይዘው ከመሄድዎ በፊት ሁልጊዜም ለእንስሳት ሃኪሙ ቀድመው ያሳውቁ።



## ያስታውሱ

የኮቪድ-19 ክትባት የኮቪድ-19 መንሰራፋትን የሚቀንስ ሲሆን፣ እርስዎን እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ የቤት እንስሳዎችዎትን ጨምሮ፣ በህመሙ እንዳይያዙ ይከላከላል። ተራዎ ሲደርስ ይከተቡ።

እንስሳቶች ሌሎች ህመሞችን ለሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ፣ ስለዚህ ከነካችኋቸው በኋላ እጃችሁን መታጠብ አስታውሱ እናም ከዱር እንስሳት ጋር ንክኪ አይፈጽሙ።



